# ከዘፀአት በፊት

## የተወደዳችሁ ወገኖቼ!

ሰሞኑን በአንዳንድ የዜና መረብ አውታሮች ላይ አንዳንድ አስተያየት ስሰጥ አንድ አንባቢ የበለጠ ነገር እንድጽፍ ስለጠየቁኝ ይህቺን ጽሁፍ አቅርቤአለሁ።የእግዚአብሔር መልካም ፈቃድ ቢሆንና ለንባብ ብትበቃ ትንሽ አሁን ስላለው የሃገራችን ሁኔታና ምን ማድረግ አለብን የሚለውን በእኔ በኩል የሚሰማኝን ለመዳሰስ እሞክራለሁ።

ተደጋጋሚ ውድቀት፣ውርደት፣ስደት፣መከራ፣ችግር እና የመሳሰሉት ነገሮች ለገጠመው አንድ ሕዝብ በነገሮች ላይ እምነት ቢያጣ አይፈረድበትም።እኛ ኢትዮጵያውያን በአሁኑ ሰአት የገጠመን ድክመት ይኼ ነው፤ በቃ እምነት የለንም ስለዚህ ሁሉ ነገር ጭልምልም ብሎ ይታየናል፤ከዛ ሁሉ ነገር ይበላሻል።ለማንኛውም ነገር ትዕግስት አስፈላጊ መሣሪያ ነው።እኔ ትዕግስትን ከመንፈሳዊ እሴቱ በላቀ መልኩ እንደ መሣሪያ እመለከተዋለሁ፤ ትዕግስት ያለው ሰው የጊዜን ትርጉም በደንብ ሊገነዘብ ይችላል።አሁንም ደግሜ ልለው የምችለው ነገር ቢኖር ትዕግስት ያለው ሰው ሁሉንም በጊዜው ያገኘዋል፤መሆን ከሚፈልገው ነገር የሚያዳግተው ምንም ነገር የለም። እንደ ሕዝብም የአሸናፊ ሕዝብ ትልቁ መገለጫው ትዕግስታዊ ፅናቱ ነው።ስለዚህ ለአንድ ሕዝብ እምነትና ትዕግስት ወሳኝ ከድል ማድረሻ መሳሪያዎች ናቸው።
እምነት ሲኖርህ ነው በትዕግስት የምትጠብቀው እንዲሁም ትዕግስት ሲኖርህ ነው የእምነትህን ውጤት የምታየው።ከዚህ በኋላ ነው ታዲያ ወደ አምላክህ የምትጠጋው፣እነዚህን ነገሮች ይዘህ አምላክህን ተስፋ ካደረግከው በእርግጠኝነት ከተነሳህለት ዓላማ ትደርሳለህ።

እኛ ኢትዮጵያዊያን በአሁኑ ሰአት እንዲህ እያልን ነው፤
አቤቱ! የሆነብንን አስብ፣ ተመልከት ስድባችንንም እይ። ርስታችን ለእንግዶች፣ቤቶቻችን ለሌሎች ሆኑ። ድሃ አደጎችና አባት(መልካም መሪ) የሌለን ሆነናል፤ እናቶቻችን እንደ መበለቶች ሆነዋል። ዉሃችንን በብር ጠጣን፣ እንጨታችን በዋጋ ገዛን። አሳዳጆቻችን በአንገታችን ላይ ናቸው፤ እኛ ደክመናል፣ እረፍትም የለንም። ለሌሎች እንግዳ ሕዝቦች (አረቦች፣አውሮፓውያን የመሳሰሉት) እንጀራ እንጠግብ ዘንድ እጅ ሰጠን። አባቶቻችን ኃጢአትን ሠሩ፤ ዛሬም የሉም፤ እኛም በደላቸውን ተሸከምን። ባሪያዎች ሠልጥነውብናል፤ ከእጃቸው የሚታደገን የለም። ከምድረ በዳ ሰይፍ የተነሣ በሕይወታችን እንጀራችንን እናመጣለን። ከሚቃጠል ከራብ ትኩሳት የተነሣ ቁርበታችን እንደ ምድጃ ጠቆረ። በጽዮን ሴቶችን

በኢትዮጵያም ከተሞች ደናግልን አጎሰቆሉ። አለቆች በእጃቸው ተሰቀሉ፤ የሽማግሌዎች ፊት አልታፈረም። ሽማግሌዎች ከአደባባይ ጎልማሶችም ከበገናቸው ተሻሩ።የልባችን ደስታ ቀርቶአል፤ ዘፈናችን ወደ ልቅሶ ተለውጦአል። አክሊል ከራሳችን ወድቋል።ኃጢአት ሰርተናልና ወዮልን! ስለዚህ ልባችን ታሟል፤ ስለዚህም ነገች ዓይናችን ፈዝዞአል፤ ስለ ጽዮን ተራራ (ቤተክርስቲያን) ባድማ ሆናለችና ቀበሮዎችም ተመላልሰውባታልና፤
አቤቱ! አንተ ለዘላለም ትኖራለህ፤ ዙፋንህ ከትውልድ እስከ ትውልድ ነው። ስለምን ትረሳናለህ? ስለ ምንስ ለረጅም ዘመን ትተወናለህ? አቤቱ ወደ አንተ መልሰን እኛም እንመለሳለን፤ ዘመናችንን እንደ ቀድሞ አድስ። ነገር ግን ፈጽመህ ጥለኸናል፤ እጅግ ተቆጥተኸናል። (ሰቆቃው ኤር 5)

ከላይ የተጠቀሰው በርግጠኝነት እኛ ላለንበት ሁኔታ ትክክል ማሳያ ነው። የእኔም ትልቁ የጽሁፌ መነሻም ለዚህ ሁሉ ነገር መፍትሔው ወደ ሃገራችን ዘጸአት አድርገን ወደ ቀድሞ ማንነታችን መመለስ አለብን ነው።ለዚህም ዘጸአት የምናደርግበትን መንገድ መጠቆም ከዚያም አልፎ አብሮ መፍትሔ መፈለግ ነው።

ከምናደርገው ዘጸአት በፊት ጠንካራ መንፈሳዊ ዝግጅት ያስፈልገናል፤ በመንፈስ የታጀበ ነገር ሁሌም ውጤቱ አስተማማኝ ነው። ጌታችንና መድሃኒታችን እየሱስ ክርስቶስ ለደቀመዛሙርቱ እንዲህ ብሏቸው ነበር፤ «እኔ ወደ አባቴና ወደ አባታችሁ ሄጄ የሚያግዛችሁን የሚያጽናናችሁንና እስከ አለም ዳርቻ በስሜ ብዙ ታምራትን እንድታደርጉ የሚመራችሁን ቅዱሱን የእውነት መንፈስ እስክልክላችሁ ድረስ በእየሩሳሌም ቆዩ» እኔም እንደ እኔ በስደት ለሚኖሩ ወንድሞቼና እህቶቼ የምላቸው ነገር ቢኖር በስደት ከአሁን በኃላ የምንቆየው ቢበዛ ለአንድ አመት ብቻ መሆን አለበት፤ ይህም ጊዜ እራሳችንን ከታላቁ ዘጸአት በፊት በመንፈሳዊ እሴት የምንዘጋጅበት ጊዜ ሊሆን ይገባዋል።

ከሁሉም በላይ ከማንኛውም የፖለቲካ አመለካከት የራቀና በሃገር ወዳድ ኢትዮጵያዊያን የተዋቀረ አንድ አስቸኳይ ግብረ ሃይል በኮሚቴ መልክ መዋቀር አለበት፤ እናም ይኼ ስብስብ በመጀመሪያ በውጪ በመላው አለም ተበትነው የሚገኙትን በስደት በመከራ እና አንገትን በመድፋት ያለውን ኢትዮጵያዊ ሁሉ በመቀስቀስ ወደ ብሔራዊ መግባባት መፈቃቀርና መረዳዳት ማምጣት አለበት። በአሁኑ ሰአት የፖለቲካ፣የጎሳ፣የእምነት መለያየት የሚባለውን ነገር ሁሉም እርግፍ አድርጎ ትቶ ወደ መግባባት እና አንድ ወጥ ፍቅር መምጣት አለበት። ፍቅር ለሁሉም ነገር አስተማማኝ መሠረት ነው፤

በፍቅር በእምነትና በተስፋ መሰረቶች የተገነባ አንድነት በምንም መልኩ አይደረመስም።

ከዚህ በኋላ በዚህ ኮሚቴ አማካኝነት ይሄ የምንፈልገው ብሔራዊ እርቅና መግባባት በእግዚአብሔር መልካም ፈቃድ ወደ አንድ ምዕራፍ ከተሸጋገረ የሚቀጥለው እርምጃ በተለያዩ ንዑስ ኮሚቴዎች ይዋቀራሉ፣ እነዚህም ንዑስ ኮሚቴዎች በስደት የሚገኘው ወገናችን ወደ ሃገሩ ከገባ በኋላ በምን በምን መልኩ መሠማራት እና ሃገራዊ ግዴታውን መወጣት እንደሚኖርበት የሚያገናኝና የሚያመቻች ክፍል ይሆናል።ይህም ማለት ለምሳሌ የኢኮኖሚ፣የጤና፣የትምህርት፣ የመሰረተ ልማት፣ የሃይል፣የእርሻ ልማት፣የመኖሪያ ቤቶች እና የመሳሰሉትን ዘርፎች ባለሙያዎችን በማገናኘት የምክክር እና የመፍትሔ አቅጣጫ እንዲያስቀምጡ የሚያደርግ ይሆናል እና ከዚያም የእነዚህ ሰዎች መገናኘት ሃገራችን እስከ ዛሬ በደሃ አቅሟ ብዙ ወጪ በማውጣት ያስተማረቻቸው ልጆቿ ሃገራዊ ግዴታቸውን ለመወጣት ምቹ መንገድ ይፈጥርላቸዋል ማለት ነው።

ውድ ወገኖቼ! ከላይ እርግፍ አርገን መተው አለብን ላልኳቸው ነጥቦች ምክንያት አለኝ፤ ይኸውም ብዙ ሰዎች ያለምንም የፖለቲካ፣ የጎሳ፣ የእምነት ጣልቃ ገብነት ሃገራቸውን ማገልገል የሚፈልጉ አሉ፤ ስለዚህ በዚህ በሚፈተረው እርቅና መግባባት በተለያት አመለካከቶች ተራርቀው የነበሩ ግለሰቦችና ቡድኖችን በማቀራረብ ለሃገራቸው አስተዋጾኦ ማድረግ የሚችሉበትን መንገድ እንዲፈልጉ ከሁሉም ተጽእኖ ነፃ የሆነ እና ሃገርንና ወገንን ለማገልገል ብቻ የተዘረጋ መንገድ ሊሆን ይገባል።እዚህ ላይ ልጨምር የምፈልገው ነጥብ ደግሞ አንዳንድ ግለሰቦች ሃገራቸውንና ወገናቸውን ለመርዳትና ለማገልገል በሚጠሩበት ጊዜ አንድም ብዙ ልመናና ሙገሳ እንክብካቤ እንዲደረግላቸው አሊያም ከነጭራሹ የሃገር እና የወገን ፍቅር የጠፋባቸው እና በራሳቸው የሚቀልዱ እና ሌሎችን(ፈረንጁን) ለመምሰል በሩጫ ላይ ያሉትስ ለእነርሱ የምናጠፋው ጊዜ፣ጉልበትና ገንዘብ የለንም። ሁሉም ወገን እዚህ ጋር ማስተዋል ያለበት አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል እንዲህ ይነበባል፤«ሙሴ ካደገ በኋላ የፈርዖን የልጅ ልጅ እንዳይባል በእምነት እምቢ አለ፤ ከግብፅም ብዙ ገንዘብ ይልቅ ስለ ክርስቶስ መነቀፍ እጅግ የሚበልጥ ባለ ጠግነት እንዲሆን አስቧልና ለጊዜው በኃጢአት ከሚገኝ ደስታ ይልቅ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር መከራ መቀበልን መረጠ፤ ብድራቱን ትኩር ብሎ ተመልክቶአልና የንጉሡን ቁጣ ሳይፈራ የግብጽን ሃገር የተወ በእምነት ነበረ፤ የማይታየውን እንደሚያየው አድርጎ ጸንቶአልና።» ዕብራዊያን 11፡-24-27፤ ስለዚህ ችግርም ቢኖር፣ ውጣ ውረድ ቢበዛ የወገኑን ችግር እንደራሱ ሳያይ አንገቱን ለሚያዞር ሰው

በእግዚአብሔር ዘንድ የሚጠየቅበት ነገር እንዳለ ሆኖ እኛ ግን ከሃገር ከሃዲ ባንዳ ምንም ለይተን አናየውም፤ ለእርሱም ለወደፊቱ ቦታ የለንም።

ወገኖቼ! የምወዳቹ የሃገሬ ሰዎች ሁሉ!

የማይቻል ምንም ነገር የለም፤ አላማውን አስተካክሎ በእምነት ለተነሳ ሰው እግዚአብሔርም አብሮት ይሰለፋል።በሃገር ደረጃም ቢሆን የራሳቸውን ጥቅም በሚያስጠብቁ ሃገሮች፣መሪዎች ከምንተማመን አንድ እግዚአብሔር አይሻለንም? ሚሊዮን ግዜ እሱ ይሻለናል።
ወገን መላው የኢትዮጵያ ልጅ ሆይ!
ተነስ! በእምነት እና በተስፋ ታጠቅ! ተዘጋጅ! በወገኖችህ ፍቅር ተቃጠል! የሃገርህን ጥፋት እንዳያሳይህ እጅህን ወደ ፈጣሪ ልብህን ወደ ሃገርህ መልስ። ተንቀሳቀስ እልፍ እልፍ በል፤ አንተ ስለወገኖችህ ፍቅር ስትነሳ ሌሎች ሲሳለቁብህ አትገረም፤ ሰይጣን በቻለው ነገር ሁሉ ይዋጋሃል፤ አስታውስ አሳቾች ስንባል እውነተኞች ነን፤ የምንሞት ስንመስል ሕያዋን ነን፤ የተቀጣን ስንሆን አንገደልም፤ ኃዘንተኞች ስንሆን ዘውትር ደስ ይለናል፤ ድሆች ስንሆን ብዙዎችን ባለ ጠጎች እናደርጋለን፤ አንዳች የሌለን ስንሆን ሁሉ የእኛ ነው።ስለዚህ በእምነት ካልተነሱ ሰዎች ጋር በማያምች አካሄድ አትጠመድ፤ ብርሃን ከጨለማ ጋር ምን ኅብረት አለው?
ይሄ የእግዚአብሔር ጥሪ ነው፤ እኔ ከሁላችሁ በትምህርትም በእድሜም የማንስ ልሆን እችላለሁ፤ እንደ እናንተም ነገር አሳምሮ ማቅረብ አልችል ይሆናል፤ ነገር ግን ስለ ሃገሬ፣ስለ ለምለሚቱ ምድር ስለ ቅኖቹ ሃገር፣ ስለ የጥቁር ሕዝብ አለኝታ፣ ስለ ቅድስቲቱ ሃገር ዘውትር አለቅሳለሁ።
አሁንም ቢሆን ለሚያምን ሁሉ ይቻለዋል፣ ሁሉም ይከናወንለታል፣ ከእኛ የሚጠበቀው ማመን ብቻ ነው፤ እውሩስ የበራለት በማመኑ አይደል? ሴትየዋስ ደሟ የቆመው በእምነቷ አይደለም? ብዙዎችስ ታላላቅ ነገሮችን የፈጸሙት አምነው ስለተነሱም አይደል?

የቴዲ አፍሮን «ወደ ሃገር ቤት» እና «ያስተሰርያል» የሚሉትን ዘፈኖች ለሁሉ ወገኖቼ እንደ መድሃኒት እንክብል ትሁንና ሁሉ ይስማው አሁንም!!

እግዚአብሔር ሃገራችንና ወገናችንን ይጠብቅልን፤ እጅግ በጣም እወዳች□ለሁ፤ ቸሩ ፈጣሪያችን ፍቅር አንድነት ይስጠን።
ክብር ለእግዚአብሔር አሁንም ለዘላለምም ይሁን፤

ወንድማችሁ